የሰ/መ/ቁ. 57114

ግንቦት 3 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፣** ሐጐስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሳ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች፣** ወ/ሮ ሃና ፀጋዬ ጠበቃ አሰፋ ዝቅአርጋቸው ቀረበ

**ተጠሪ፣** ወ/ት ጣዕሙ ደስታ ጠበቃ ገመቹ ሮሮ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ይጣራ ጥያቄን መነሻ ያደረገን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሾች የነበሩት ዳዊት ፀጋዬ የተባለው የአሁንዋ አመልካች ወንድም እና አመልካች ናቸው፡፡ ክሱ በተጠሪ ላይ ሊቀርብ የቻለው የውርስ ንብረት ልታካፍል ይገባል በመባሉ ነው ተጠሪ ለክሱ በሰጠችው መልስ ክሱ የቀረበው የከሣሾች አባት ከሞቱ ከአሥር ዓመት በላይ ቆይቶ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ተከራክራለች፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ የዳዊት ፀጋዬ ሞግዚት በመሆን ያሳደገችው መሆንዋን ከመረጋገጡም በላይ እስዋም ይህን መሠረት በማድረግ በዳዊት ላይ አንስታው የነበረውን የይርጋ መቃወሚያም መተዋን እንደገለጸች የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ ላይ ተመልቶአል፡፡ ክሱ የቀረበለት ይኸው ፍ/ቤት ሁሉም ወገኖች ያሰሙትን ክርክር ከመረመረ በኃላ የአሁንዋ አመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት ጥያቄዋን ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2002 ዓ.ም በጻፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎቱ እንዲታይ የተደረገው ተጠሪ የአመልካች እንጀራ እናት መሆንዋ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦ እያለ ይርጋው በአመልካች ላይ ተፈጻሚነት አለው የመባሉን አግባብነት ሊመረመር ይገባል በመባሉ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ ግራቀኝ ወገኖች ያሰሙትን ክርክር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እና የተሰጠውን ውሣኔ ይዘት ተመልክተናል፡፡ ከዚህም በዋናነት ለመገንዘብ የቻልነው ተጠሪ የአመልካችም የእንጀራ እናት መሆንዋን ነው፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ሞግዚት የነበረችው ለዳዊት ፀጋዬ ብቻ እንጂ አመልካች በተጠሪ ሞግዚትነት ሥር

አልነበረችም፡፡ ይህም ሆኖ ግን አመልካችም እንደወንድምዋ /ዳዊት ፀጋዬ/ በወቅቱ ለአካለመጠን ያላደረሰች የነበረች ስለመሆንዋ ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ፍ/ቤቱ በተጠሪ የተነሳው የይርጋ መቃወሚያ በአመልካች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት አለው ለማለት ከበቃበት አንደኛው ምክንያትም አመልካች የሞግዚትነት እና የአሳደሪነት ሥልጣን በነበራቸው ሰዎች አማካይነት መብትዋን በወቅቱ ማስከበር ነበረባት የሚል ነው፡፡ ይህን ምክንያት መነሻ በማድረግም የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ ለይርጋው ጊዜ አቆጣጠር እንደሁለተኛ ምክንያት አድርጎ ወስዶአል፡፡ በሌላ በኩል ግን ፍ/ቤቱ የተጠሪን የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት አለው ለማለት እነዚህን ምክንያቶች መሠረት ቢያደርግም አመልካች ከሞግዚት አስተዳደር መቼ ነፃ እንደወጣች በውሣኔው ላይ አላመለከተም ተጠሪም ብትሆን የአመልካች አባት የሞቱበትን ጊዜ መነሻ በማድረግ የአሥር ዓመትን የይርጋ ጊዜ /የፍትብ/ሕግ ቁ 1845/ በመጥቀስ ከመከራከር አልፋ አመልካች ጊዜውን ያሳለፈችው ለአካለ መጠን ከደረሰች በኃላ /ከሞግዚት አስተዳደር ከወጣች በኃላ/ ነው የሚል መከራከሪያ አላነሳችም፡፡

በበኩላችን እንደምናየው የተጠሪ የይርጋ መቃወሚያ በዳዊት ፀጋዬ ላይ ተፈጻሚነት የለውም ከተባለ በአመልካችም ላይ በተመሳሳይ ሁኔታ የማይታይበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡ የአመልካች ሞግዚት ነበሩ የተባሉት ሰዎች በወቅቱ መብትዋን አላስከበሩላትም የሚለው አካሄድም እንደዚሁ የሕግ መሠረት ያለው አይደለም፡፡ ዋናው መለየት ያለበት አመልካች የሟች አባትዋ ወራሽ መሆንዋን እና ለማስከበር የተነሳችውም የወራሽነት መብትዋ እንደሆነ ነው፡፡ የይርጋው ጊዜ ሊቆጠርባት የሚገባውም በመብትዋ መጠቀም ከቻለችበት /አካለመጠን ከደረሰችበት/ ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኖአል በማለት በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ በሕጉ አተገባበር ረገድ መሠረታዊ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ በዚህ መሠረትም ተከታዩን ወስነናል፡፡

## *ው ሣ ኔ*

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 14168 መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 79963 ግንቦት 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካች ያቀረበችው የውርስ ይጣራልኝ ክስ በይርጋ ቀሪ አልሆነም ብለናል፡፡ ስለዚህም የአመልካች የውርስ ይጣራልኝ ጥያቄም ከዳዊት ፀጋዬ ጥያቄ ጋር አብሮ ይታይ በማለት ወስነናል፡፡
3. ግራቀኝ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቶአል፡፡ ይመለስ፡፡

***የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት***

ም.አ